<u>የCRBA ማመልከቻ አስገብተው ቀጠሮ ከተቀበሉ በኋላ በቀጠሮ ቀን አሚልተው መገኘት የሚገባዎት ዶክመንቶች ዝርዝር</u>

1) ፓስፓርት የሚወጣለት ልጅ ኦሪጂናል የልደት ወረቀት እና አንድ ኮፒ፣ የልደት ወረቀቱ እንግሊዘኛ ከሌለው የእንግሊዘኛ ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡
2) የአሜሪካ ዜግነት ያለው ወላጅ የአሜሪካ ዜግነት ያገኘበት ሰርቲፍኬት (Naturalization Cetificate) **ኦሪጂናል እና አንድ ኮፒ**
3) የአሜሪካ ዜግነት ያለው ወላጅ የአሜሪካ ፓስፓርት የውስጥ ገፅ ኮፒ (ስም፣ ፎቶ፣ የልደት ቀን ያለበት ገፅ)
4) የአሜሪካ ዜግነት የሌለው ወላጅ (በአብዛኛው እናት) የኢትዬጵያ ፓስፓርት ወይም የቀበሌ *መታወቂያ* **ኦሪጂናል እና አንድ ኮፒ** - የቀበሌ *መታወቂያ* እንግሊዘኛ የሌለው ከሆነ የእንግሊዘኛ ትርጉም፣ የፋይዳ *መታወቂያ* ካለም *መ*ጠቀም ይቻላል፡፡
5) የአሜሪካ ፓስፓርት የሚጠየቅለት ልጅ በጋብቻ የተወለደ ከሆነ፣ ወላጆቹ ጋብቻ የፈፀሙበት የጋብቻ ሰርቲፍኬት ኦሪጂናል፣ እንግሊዘኛ ፁሁፍ ከሌለው የእንግሊዘኛ ትርጉም አብሮ *መ*ቅረብ ይኖርበታል፡፡
6) የአሜሪካ ዜግነት ያለው ወላጅ ከዚህ በፊት ጋብቻ ከነበረው እና ፍቺ ከፈፀመ የፍቺ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣ የበፊት የትዳር አጋሩ በሞት ከተለየች የሞት ሰርቲፍኬት ማቅረብ አለበት፡፡
7) ፓስፓርት የሚወጣለት ልጅ ወላጆች ያላቸውን የፍቅር/የትዳር ግንኙነት ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋቸዋል፡፡

   <u>**በእናት በኩል፣**</u> እናት የእርግዝና ክትትል ያደረጉበት ማስረጃ፣ ከእርግዝና ክትትል ጋር ወይም ከወሊድ ጋር በተገናኘ ለሆስፒታል የተከፈለ ማንኛውም ክፍያን የሚያሳይ ደረሰኝ፣ የአልትራሳውንድ ሪፓርት/sonagram records/፣ ልጅ ሆስፒታል በሚወለድበት ጊዜ ሆስፒታሉ የሚሰጠው የልደት ማስረጃ/Birth Notification/፣ ልጅ ከተወለደ በኋላ ክትባት የወሰደበት /የክትባት *መ*ከታተያው የልጁን ስም፣ የእናትና የአባት ስም የሚያሳይ *መ*ሆን ይኖርበታል/፣

   <u>**የአሜሪካ ዜግነት ባለው ወላጅ በኩል፣**</u> ወደ ኢትዬጵያ በሚመላለስበት ጊዜ ኤርፓርት ላይ ፓስፓርቱ ገፅ ላይ የሚመታውን የመውጫና የመግቢያ ማህተም /Entry & Exit Stamp/ ኮፒ፣ ለሚስቱ ወይም ለልጅ እናቱ እና ለልጁ የሚያደርገውን የገንዘብ ድጋፍ/ገንዘብ የተላከበት ደረሰኝ፣ ከሚስቱ፣ እጮኛው፣ የልጅ እናቱ ጋር በቴሌግራም/ዋትስአፕ/ሜሴንጀር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ Chat History ኮፒ፣ ወላጆች (ትዳር ካለ) የጋራ ንብረት ወይም የጋራ የባንክ ሂሳብ ካላቸው ማስረጃ፣

   ፎቶዎች፣ የሠርግ ፎቶ፣ ወላጆች በሚዝናኑበት ጊዜ የተነሱት ፎቶ /Honeymoon/፣ ልጅ ከመረገዙ በፊት የተነሱት ፎቶ፣ በእርግዝና ወቅት የተነሱት ፎቶ፣ በወሊድ ጊዜ የተነሱት ፎቶ፣ ከእርግዝና በኋላ የተነሱት ፎቶ፣ የአሜሪካ ዜግነት ያለው ወላጅ ከልጁ ጋር የተነሳው ፎቶ፣

8) የአሜሪካ ዜግነት ያለው ወላጅ ፓስፓርት የሚጠየቅለት ልጅ ከመወለዱ በፊት በአሜሪካ ቢያንስ ለ5 ዓመታት መኖሩን የሚያሣይ ማስረጃ (Proof of five years physical presence in the US)፣

   እንደማስረጃ ሊያገለግሉ የሚችሉ፤

   - W-2 Form (for employed/ተቀጥረው ለሚሰሩ) 1099 (for self-employed/ በግል ለሚሰሩ)፣
   - ትምህርት ቤት/ኮሌጅ ገብተው የነበሩ ወላጆች ከሆኑ - የትምህርት ማስረጃ፣ ትራንስክሪፓት፣ ለትምህርት ክፍያ የተከፈለበት፣ ሰርቲፍኬት፣ ወዘተ
   - የመኖሪያ አፓርትመንት ተከራይተው የሚኖሩ/ሲኖሩ የነበረ ከሆነ - Rental Lease Agreement፣ በራሳቸው ቤት የሚኖሩ Mortgage የተከፈለበት፣ Property Tax የተከፈለበት፣ ወይም የ Mortgage ውል የተያዘበትን ሰነድ ማቅረብ ይቻላል፣
   - Employment Verification Letter - በቅጥር በስራ ላይ የቆየ መሆኑን ከቀጣሪ የሚሰጥ ደብዳቤ - ከዚህ ቀን እስከዚህ ቀን መስራታቸውን የሚገልፅ ደብዳቤ፣
   - Pay Stubs/Earning Statements

- Utility Payments (የፍጆታ አገልግሎት ክፍያዎች) Bills – Electric Bills/ የመብራት፣ Water Bills/ የውሃ፣ House Gas Bills/ የጋዝ፣ Waste Collection Bills, ወዘተ
- Bank Statements (ባንክ ሰቴመንት እንደ ማስረጃ ማቅረብ የፈለገ፣ የሁሉንም ወራት ማቅረብ አያስፈልግም - ለምሳሌ ዓመቱ 2021 ቢሆን - የሁለት ወር የMarch 2021 እና የSeptember 2021 ወይም የJanuary 2021 እና የJune 2021 ሊቀርብ ይችላል።)
- Vehicle Registration – DMV የሰጠው የተሽከርካሪ የምዝገባ መረጃ፣
- ኢንሹራንስ - የህክምና ወይም የመኪና ኢንሹራንስ፣

ከላይ ከተዘረዘሩት ማስረጃዎች በተጨማሪ እንደ አመልካቹ የስራ እና የኑሮ ሁኔታ አማራጭ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይችላል። ለምሳሌ፣

- Truck Driver የሆነ ሰው የToll Road ደረሰኝ ቢያቀርብ እንደ ማስረጃ ይያዛል፣
- ለህክምና ምርመራ ወደ ህክምና ተቋም የሄደ ሰው የላብራቶሪ ምርመራ ውጤት ወይም ምርመራ ማድረጉን የሚያሣይ ማስረጃ ማቅረብ ይችላል።
- በስራ ቦታ ላይ የሚሰጥ ሰርቲፍኬት ለምሳሌ Certificate of Appreciation አንደ ማስረጃ ሊቆጠር ይችላል።

ትከሩት የሚሹ ጉዳዬች፣

- የታክስ ሪፓርት (Form 1040/IRS transcripts) እንደማስረጃ አይቆጠርም፣
- ለማስረጃ የሚቀርበው ማንኛውም ዓይነት ዶክመንት - የሰውየው ስም፣ አድራሻ እና ቀን/ዓመት ያለው መሆን ይኖርበታል።
- የሚጠየቁት የአምስት ዓመት ማስረጃዎች ለተከታታይ አምስት ዓመታት የግድ መሆን የለባቸውም። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው አሜረካ ከ2012 ዓመት ጀምሮ መኖር የጀመረ ቢሆንና ልጁ የተወለደው በ2023 ቢሆን ከ2022 ዓም ጀምሮ ወደኋላ እስከ 2012 ዓ.ም ድረስ ባሉት አምስት ዓመታት /ለተከታታይ ዓመታት ባይሆንም/ ዶክመንቱን ማቅረብ ይችላል።

ፎርሞችና ሌሎች፣

- DS-11 (የፓስፓርት ማመልከቻ ፎርም፣ ኖቶራይዝ መደረግ አያስፈልገውም።)
- DS-3053 (ሁለቱም ወላጆች በኢንተርቪው ቀን የማይገኙ ከሆነ፣ የማይገኘው ወላጅ ለሚገኘው ወላጅ ውክልና የሚሰጥበት ፎርም ነው፣ ኖቶራይዝ መደረግ አለበት፣ የሚያገለግለው ለ90 ቀናት ብቻ ነው።)፣ የ DS-3053 የውክልና ፎርም ኦሪጂናል እና ውክልናውን ሲፈርም ያሳየውን የመታወቂያ ዓይነት (State ID, Driving License, Passport) ኮፒ አያይዞ ማቅረብ አለበት፣
- DS-5507 (የአሜሪካ ዜግነት ያለው ወላጅ አሜሪካ የኖርበትን ጊዜ የሚያሳይ ፎርም ነው፣ ኖቶራይዝ መደረግ አለበት፣ የጊዜ ገደብ የለውም/ አንዴ ኖቶራይዝ ከተደረገ በማንኛውም ጊዜ ተቀባይነት አለው፣) የአሜሪካ ዜግነት ያለው ወላጅ በኢንተርቪው ጊዜ የሚገኝ ከሆነ አስቀድሞ ኖቶራይዝ ማድረግ አያስፈልገውም፣ ኢምባሲ በኢንተርቪው ጊዜ ኖቶራይዝ ማስደረግ ይችላል።
- 5cm X 5cm የሆነ የፓስፓርት አመልካቹ ልጅ ፎቶ፣
- 135 $ ክፍያ - በኢትዬጵያ ብር በካሽ መክፈል ይቻላል - /ኢምባሲው በሚጠቀምበት ቁርጥ የምንዛሬ ተመን 162.00 ብር ሂሳብ 21,870.00 ብር እና በተጨማሪ የፓስታ ክፍያ 200.0 ብር በጠቅላላው 20,070.00 ብር ማዘጋጀት አለበት። በCredit Card ወይም Debit Card መክፈል ይቻላል፣ የሞባይል ባንክ ክፍያ ተቀባይነት የለውም።

If you need further assistance or clarification, call Abraham at 0911502432/0903558877.